ፓኖራማ ቁጥር 59

የትዝብት አድማስ

የካቲት 1 ቀን  2001  ዓም

## <u>የሶማሊያ ጉዳይ</u>

ባለፈው ሳምንት ሸህ  ሸሪፍ  ሸህ አህመድ የተሰኘ የአርባ አራት ዓመት ጎልማሳ የሶማሊያ ፕሬዝዳንት ሆኖ መመረጡን በርካታ  የብዙሃን  መገናኛ አውታሮች ተናግረውታል፡፡ የምርጫው ሥነርዓት የተፈፀመው በሶማሊያ ሳይሆን በጅቡቲ ከተማ እንደነበርም ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሶማሊያ ከአውሮፓውያን የቅኝ  ግዛት ነፃ  ከወጣችበትም  ከስድሳዎቹ  ዓመታት  ጀምራ  በርካታ  ፕሬዝዳንቶች መፈራረቃቸው የታወቀ ቢሆንም፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን  የሶማሊያን የውስጥና የውጭ ፖለቲካ በቅርብ የመከታተል ተግባሯና ግዴታዋ እንደሆነ ይሰማታል፡፡ ለዚህም የራሷ ምክንያት ነበራት፡፡ያ ምክንያት አሁንም ህያው ነው፡፡ ይህ ምክንያትም የህልውናዋ ጉዳይ በመሆኑ፥ በሶማሊያ  የሚፈራረቁትን መሪዎች ባኅርይ ፥ፖሊሲ፥ የመንግሥት  ይዘትና  አቅጣጫ  በቅርብ  ለመከታተል ትገደዳለች፡፡  ሶማሊያ ነፃ ከወጣችበት ዘመን  ጀምሮ  እስካሁኑ ወቅት  ድረስ በርካታ መሪዎችና አስተዳደሮች ቢቀያየሩም ፥  እናም ደግሞ አንዱ ከሌላው የሚለየው፥ ርዕዮተ-ዓለምና የአስተዳደር  ዘይቤ  ያለው  መስሎ  ለመታየት ቢጥርም፥ ሁሉም  የሚስማማበት  ግን አንድ  መሠረታዊ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም ሀገር የማስፋፋት ፖሊሲና የጎረቤት ሀገራት   መሬቶችን   በጦርነት የመያዝ አባዜ ነው፡፡ ይኸ የጎረቤት ሀገሮችን መሬቶች   በጦርነት  የመንጠቅ ፖሊሲ፥በብዛት ሙከራ የተደረገው፥ የኢትዮጵያን ምሥራቃዊ ግዛት የሆነውን የኦጋዴንን  መሬት  ለመውሰድ የተደረጉት ሙከራዎችና ኢትዮጵያም ጥቃቱን ለመከላከል  ብዙ  ጀግኖቿን   ያጣችባቸው  ውጊያዎች  ናቸው፡፡  በሶማሊያ ህገመንግሥት የተጻፈውና በሰንደቅ ዓላማዋ  ኮከብ ላይ ያሉት አምስት ነጥቦች በጎረቤት ሀገሮች  የሚኖሩትን  ሶማሊዎች ሁሉ  በአንድ ላይ ለማሰብሰብ ዓላማ

ያደረገ የማይሻር፥ የማይገሰስና የማይሰረዝ የሶማሊያ መሪዎች እምነትና አቋም ሆኖ የኖረ ነው፡፡ አሁን የተመረጠውም ሰው የፕሬዝዳንትነት ቃለ መሃላውን ሲያደርግ ይህንኑ በተግባር ለመተርጎም እንደሚጥር እኛ ልንዘናጋ እንችልም፡፡ ከወያኔ በፊት የነበሩት ሁለቱ የኢትዮጵያ ተፈራራቂ ሥርዓቶች በግዛት ዘመናቸው ወቅት የሶማሊያ ተስፋፊ መሪዎች በየጊዜው ያነሷቸውን የወረራ ጦርነቶች ፥ እንዳመጣጣቸው ሊያመክኗቸው የቻሉት፥ በዘመናቸው ከፍተኛ መሥዋዕት በከፈለው የመከላካያ ሠራዊት የህገርና ሕዝብ ፍቅር ስሜት እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡ በ1928 የኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ በነበረው የወልወል ግጭት ላይ የአርበኝነት ተግባር ቆራጥነትን ያሳየው የኢትዮጵያ ጀግና ሕዝብ በኩራት የሚጠቀስ ነው፡፡ ከዚያ ታሪካዊ ወቅት ጀምሮ እስከ ትላንቱ የደርግ ዘመን ድረስ የተለያየ የጦርነት ደረጃ ያካተቱ የሶማሊያን የመስፋፋት ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የተካሄዱት ውጊያዎች በአቸናፊነት ያመከነው፥ በወቅቱ ጀግናው ሕዝባችን መሆኑ የሚካድ አይሆንም፡፡ ይህንን መጥቀሳችን ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ስለአሉን ነው፡፡ አንደኛው የዚያን ጀግና ሕዝብ መስዋዕትነት በአጋጣሚ ለማስታወስ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የአሁኑና ተተኪው ትውልድ ታሪክን እያስታወሰ በስንት ጀግኖች ደምና አፅም የግዛት አንድነቷንና ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችውን ሀገሩን፥ ዛሬ የወያኔ መሪዎች እንዴት ሊፈረካክሷት እንደቻሉ ለማስታውስ ብለን ነው፡፡ "ፍርድ ለግጫ ነው" እንደሚባለው ፥ የሀገራችንን ጉዳይ ግጫ ፍርዱን እየሰጠ፥ ለታሪክ እንዲያስ መዘግብ እንፈልጋለን፡፡ ምክንያቱም የሀገራችን ታሪክና ጎልውና በዘረኞች ደባና ተንኮል ተድበስብሶና ጠፍቶ እንዲቀር ስለማንሻ ነው፡፡

የወቅቱ የሶማሊያ የፖለቲካ ገፀ-ምድር በተለያዩ ነፍጥ በአነገቡ ቡድኖች እየታመሰ ያለ መስሎ ብታይም፥ እናም ታዲያ ፥ ሁላቸውም የየራሳቸውን የተለያየ ፍላጎትና ርዕዮት ለማሳካት ሲሉ እሳትና ገለባ መስለው ለመታየት ቢጥሩም ፥ የሶማሊያ መሪዎች ኢትዮጵያን እንደ ዋና ጠላት ፈርጀው የሶማሊያን ሕዝብ በማያቋርጥ የጦርነት ሥነአዕምሮ ውስጥ እንዲኖር በማድረግ

ተግተው ይሰራሉ:: አመች ጊዜ እየጠበቁም ዓላማቸውን ለመፈፀም ፥ በህገ መንግሥታቸው ውስጥ የተጻፈውንና በስንደቅ ዓላማቸው ላይ የተለጠፈውን ምኞት ለማሳካት በጋራ የሚጥሩ ናቸው:: በወያኔ መሪዎችና በሶማሊያ መሪዎች መካከል አንድ ልዩነት አለ ከተባለ፥ ሶማሊያ "የተበታተነውን" የሱማሊያን ዘር መሰብሰብ አለብን ብለው ተግተው ሲሰሩ ፥ የወያኔ መሪዎች ግን፥ በዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ ለመበታተንና ሀገሪቱንም ለመገነጣጠል ያለማቋረጥ መፍጨርጨራቸው ነው::ሶማሊዎች የሀገራቸውን ግዛት ለማስፋፋት እንዲችሉ የህግ ግዴታ በህገ መንግሥታቸው ቀርፀው ተግባራዊ ለማድረግ ቃለ መሃላ ሲወስዱ፥ ወያኔዎቹ ደግሞ አብሮ ለዘመናት የኖረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ተገነጣጥሎ በየአቅጣጫው እንዲሄድ የሚገፋፋውን የህግ አንቀጽ ( 39 አንቀጽ) በህገመንግሥት የሚቀርጹ ጉደኞች ናቸው:: ይህ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በመሠረታዊ ገፅታው ወያኔዎቹና የሶማሊያ መሪዎች የሚያስማማቸው ሀቅ ቢኖር ደግሞ፥ ሁለቱም ኢትዮጵያንና ዜጎቿን መጥላታቸውና መፍራታቸው ነው:: የወያኔ መሪዎች፥ባልቸገራቸውና በማያገባቸው ጉዳይ በመዘፈቅ፥የበላይ አለቆቻቸውን የውጭ ፖሊሲ ተልእኮ ለመፈፀም በታዘዙት መሠረት የሀገሪቱን የመከላካያ ሠራዊት ወደ ሶማሊያ ግዛት በመላክ የብዙ ሰው ሕይወት እንዲጠፋ አድርገዋል:: በትክክል ለመገመት የማይቻል ሀብትና ንብረት አውድመዋል :: አንድ ነፃ ሀገር ሊኖረው የሚገባውን የገለልተኝነት ፖሊሲና የዓለም-አቀፍ ደንቦችን፥ ስምምነቶችንና ሕግጋትን በመጣስ፥ ሀገራችን ከጎረቤቶቿ ጋር ሊኖራት የሚገባትን መልካም ግንኙነት በደም በክለዉታል:: ይህም ለአዲሶቹ የሶማሊያ መሪዎች ሕዝባቸውን ለማስተባበር የሚያስችላቸውን ማጠየቂያ አስገኝተውላቸዋል:: የወያኔ ወረራ ግን ለሕዝብ ያስገኘው ምንም ጥቅም የለም:: ለወያኔ የአሜሪካንን እርዳታ ከማዡግድጎዱ በቀር:: ሀገራችን ጠላት አንኳታል የተባለ ይመስል የአንድ ልዕለ ኃያልን የውጭ ፖለሲ ዓላማ ለማስፈፅም ሲባል ብቻ፤የሀገራችንን ታሪክና ክብር ዝቅ በሚያደርግ የተላላኪነት ሥራ መስራት የሚያዋርድ እንጅ በዓለም አቀፍ ኅብረተስብ ዘንድ የሚያስከብር አይደለም:: ያም ሆኖ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ ቢሆን ኖሮ እንኳ ባለከፋም ነበር::

ግን አንዳችም ለሀገር የሚጠቅም ነገር የሚያመጣ እንዳልሆነ ብንገነዘብም ወያኔ ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ስለማይሰራ ደግሞ ከቶ አንደነቅም።

ኢሕአፓ፥ የወያኔን በሶማሊያ ውስጥ ጣልቃ የመግባቱንና ስለፈሰሰው የንፁኃንን ደም ምክንያት የሆነውን ጦርነት ሲያወግዝና ሲቃወም የነበረ መሆኑ በታሪክም ያስመዘገበ መሆኑን ያስታውሳል ። ይህ የፓርቲ አቋም እንደተጠበቀ ቢሆንም፥ በሃይማኖት ፅንፈኝነት ላይ የተመሠረተው አዲሱ የሶማሊያ አስተዳደር፥ ለአካባቢው ሠላምና መረጋጋትን ያመጣል ብለን አናስብም። በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን ቋሚ አቋም ይለውጡታል ብለንም አንጠብቅብም ። ዛሬ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ሀገራዊ መንግሥት ስለሌለ፥ ይኸ ባለፈው ሳምንት ሥልጣን የያዘው የሸኽ ሸሪፍ አህመድ ሸሪፍ ቡድን በአክራሪ የሃይማኖት ጽንፈኝነት የተመረዘውን ዓላማውን ለማስፈፀም እንደሚንቀሳቀስ ልንስተው አንችልም። ለነገሩ በዚሁ በአዲሱ አስተዳደር ላይ የባሱ ፅንፈኞች ተባብረው ተነስተውበታል። የሶማሌ ሕዝብ ለሰላም አልታደለም።በመሆኑም የአፍሪካ ቀንድ ትርምስ ቀጣይ እንጂ የሚቆም አይመስልም።

**የወያኔ መሪዎች በየጊዜው በየቦታው ጦርነት የመጫር አባዜ በሁለት ቋሚ ፖሊሲዎች ላይ የተመሠረተ ነው። አንደኛው ከአምባገነን ባኅርይ የመነጨ ሆኖ፥ በመሪር አገዛዛቸው ምክንያት የተንገፈገፈው ሕዝብ እንዳይነሳባቸው፥ የተቃውሞውን አቅጣጫ ለማሳትና የትግል ትኩረቱንም ለማኮላሸት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የበላይ ጠባቂዎቻቸውን ትዕዛዝ እያሟሉ ፥ ለዕድሜያቸው መቀጠያ የሚረዳቸውን ድጋፍ ለማግኘት ነው። ሁለቱም ለጊዜው ሊይዙላቸው ይችሉ ይሆናል። በዘለቄታ መልኩ ግን ከማይቀረው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና የፍርድ ውሳኔ ሊያድናቸው አይችልም። የበላይ ጠባቂዎቻቸው መለዋወጥም የተመኙትን ያህል እንደማይረዳቸው ለማንም የተሰወረ አይሆንም።**

የጎረቤት ሀገራትን አስመልክቶ ፥ ሀገራችን ሊኖራት የሚገባውን የውጭ ፖሊሲና የምትከተለውን መመሪያ ኢሕአፓ እንደ አስፈላጊነቱ በመርኅ ደረጃ ሲታገልበት መቆየቱ ድብቅ አይደለም። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከማንኛው ሀገር ጋር ሊኖራት የሚችለው ግንኙነት በዕኩልነት፥ በጋራ ስምምነትና በመከባበር ላይ ሆኖ፥በተለይ ከጎረቤቶቿ ጋር ደግሞ የነርሱን ጥቅምና ኅልውና ሳትጋፋ፥ የራሷንም ነፃነት ሳታስደፍር በሰላም አብሮ መኖር ነው። የሀገራችን የውጭ መመሪያ፥በሀገራችን የውስጥ አስተዳደር ላይ የተመሠረተ መሆን ስለሚገባው፥ ሀገራችን ከጎረቤት ሀገሮችጋር በሠላም ለመኖር ካስፈለጋት፥መጀመሪያ የራሷን የውስጥ ሠላምና መረጋጋት መኖሩን ማረጋጥ አለባት። ይህ ሊመጣ የሚችለው ደግሞ፥የዴሞክራሲ ሥርዓት በአስተማማኝ መልኩ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል። የዴሞክራሲ ሥርዓትን አስተማማኝ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ ፥ አሳታፊ **ዲሞክራሲ እንዲኖር የግድ ይላል**።ይኸ ደግሞ የወያኔ መሪዎች በምኒልክ ግቢ መሽገው እያሉ ሊመጣ አይችልም።

በሶማሊያ፥አደም አብዱሌ ኡስማን፥ በአሊ ሸርማርኬ፥አሊ ሸርማርኬ፥ በስያድ በሬ፥ዚያድ በሬ በአብዱላሂ ዩሱፍ ዛሬ ደግሞ በሸኽ አህመድ ሸሪፍ ቢለዋወጡ የሀገራችንን የግዛት አንድነት አክብረው፥ የመስፋፋት ህልማቸውን ይሰርዛሉ ብለን አናስብም ። አንጠብቅምም። ታዲያ ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬም እንደ ጥንቱ፥ የግዛት አስፋፊዎችን እየተከላከለች በማባረር፥ በአስተማማኝ ደረጃ ዋስትና ያለውን የግዛት አንድነቷንና የነፃነት ልዕልናዋን ለመጠበቅ፥ ፀረ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ የሆኑትን የወያኔ መሪዎች፥ ሀገር ወዳድነታቸው ጥያቄ ውስጥ በማይገባ መሪዎች መተካት ወሳኝ ፥ አንገብጋቢ ፥ አጣዳፊና ብሔራዊ ተግበር ነው ። ይህ ደግሞ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ አምርረንና ቆርጠን በወያኔ አገዛዝ ላይ መነሳት አለብን። ሌላ መፍትሄ የለም።